EXAM READY ENVIRONMENTAL SCIENCE



6



ለፈተና ዝግጁ አካባቢ ሳይንስ

Grade 6 Environmental Science

ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር የሚጣጣም፤ ዋና ሐሳቦች፣ ምሳሌዎች፣ ምዕራፍ ፈተናዎችና 3 ሞዴል ፈተናዎች



6ኛ ክፍል

ERMIAS WEDAJE TEGBARU

ለፈተና ዝግጁ አካባቢ ሳይንስ

6ኛ ክፍል · Exam Ready Environmental Science Grade 6

የጥናት መመሪያ፣ የተሠሩ ምሳሌዎችና የመለማመጃ ፈተናዎች

Ermias W. Tegbaru (Eng.)

© 2026 Ermias W. Tegbaru። መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው። ያለ ደራሲው የጽሑፍ ፈቃድ የዚህን መጽሐፍ ማንኛውንም ክፍል መቅዳት፣ ማጋራት ወይም መሸጥ አይፈቀድም።

ይህ ራሱን የቻለ የጥናት መመሪያ ነው። በአዲስ አበባ ጥቅም ላይ የሚውለውን የ6ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ሥርዓተ ትምህርት ይከተላል፤ ሆኖም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ወይም የትምህርት ሚኒስቴር ይፋዊ ሳትመት አይደለም። ሁሉም ማብራሪያዎች፣ ምሳሌዎችና ጥያቄዎች አዲስ የተዘጋጁ ናቸው።

እውነታዎቹ ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር አንድ በአንድ ተነጻጽረዋል፤ እያንዳንዱ የመልስ ቁልፍም በኮምፒዩተር ተረጋግጧል። ስሕተት ካገኛችሁ በሚቀጥለው እትም እንዲታረም እባካችሁ ለደራሲው በቴሌግራም (@Ermias_Wedaje) አሳውቁ።

የመጀመሪያ እትም፣ 2026 (2019 ዓ.ም)።

መጽሐፉን እንዴት ትጠቀሙበታላችሁ?

እያንዳንዱ ምዕራፍ ተመሳሳይ አደረጃጀት አለው፤ ስለዚህ ምን የት እንደሚገኝ ሁልጊዜ ታውቃላችሁ። እያንዳንዱ ምዕራፍ በ«**ይህ ምዕራፍ በፈተና እንዴት ይመጣል?**» ሳጥን ይጀምራል፤ **Exam Booster** የሚል ምልክት ያላቸው ምሳሌዎች በሞዴል ፈተናዎች ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚመጡ የጥያቄ ዓይነቶችን ያሳያሉ።

ዋና ዋና ሐሳቦች
የክፍሉ ደንቦችና እውነታዎች፣ በአጭሩና በግልጽ።

የተሠሩ ምሳሌዎች
የፈተና ዓይነት ጥያቄዎችና መፍትሔዎቻቸው። መፍትሔውን ሸፍናችሁ መጀመሪያ ሞክሩ።

ተጠንቀቁ!
ተማሪዎች ብዙ ጊዜ የሚሠሯቸው ስሕተቶችና ትክክለኛው መንገድ።

መልመጃ
ደረጃ 1 መሠረታዊ · ደረጃ 2 መካከለኛ · ደረጃ 3 ፈታኝ።

የፈተና ዓይነት ጥያቄዎች
በ6ኛ ክፍል ፈተና አቀራረብ የተዘጋጁ 20 ምርጫ ጥያቄዎች።

ለመምህሩ
ጊዜ፣ መነሻ እንቅስቃሴዎች፣ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች፣ እንቅስቃሴዎችና ምዘና።

መጽሐፉን እንዴት ትጠቀሙበታላችሁ? (ቀጣይ)

ለተማሪዎች

- በገጽ 6 ላይ ባለው **የመነሻ ፈተና** ጀምሩ። የትኞቹ ምዕራፎች ብዙ ሥራ እንደሚያስፈልጋቸው ያሳያል።
- ዋና ሐሳቦቹንና ምሰሎቹን አንብቡ፤ ከዚያ እያንዳንዱን ምሳሌ መፍትሔውን ሸፍናችሁ ሥሩ።
- የእያንዳንዱን ክፍል የደረጃ 1 እና 2 መልመጃዎች ሥሩ፤ ዝግጁ ስትሆኑ ደረጃ 3ን ሞክሩ።
- የምዕራፉን ፈተና በ30 ደቂቃ ሥሩ፤ በምዕራፉ መጨረሻ ባሉት መልሶች አርሙ፤ የተሳሳታችሁትን ሁሉ እንደገና ሥሩ።
- በመጨረሻዎቹ ሳምንታት የቁልፍ እውነታዎች ገጹንና የ20ዎቹ ሰሕተቶች ገጽን አጥኑ፤ ሦስቱን ሞዴል ፈተናዎች (40 ጥያቄ፣ 1 ሰዓት) ሥሩ። የመልሰ ቁልፎቹ እያንዳንዱ ጥያቄ ከየትኛው ምዕራፍ እንደሆነ ያሳያሉ።

ለመምህራን

- እያንዳንዱ ምዕራፍ የመማሪያ መጽሐፉን ክፍሎች ይከተላል፤ ስለዚህ ከትምህርታችሁ ጋር አብሮ መጠቀም ይቻላል።
- «ለመምህሩ» ገጽ የሚመከር የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ የ5 ደቂቃ መነሻ እንቅስቃሴዎች፣ የተለመዱ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችና ማሰተካከያቸው እንዲሁም የእንቅስቃሴ ሐሳቦችን ይሰጣል።
- የምዕራፍ ፈተናዎቹንና ሞዴል ፈተናዎቹን እንደ ክፍል ፈተና መጠቀም ይቻላል፤ የመልሰ ስንጠረጉቹ ለእያንዳንዱ መልሰ አጭር ምክንያት ይዘዋል።

ለወላጆች

- ልጆችሁ በየቀኑ አንድ የተሠራ ምሳሌ እንዲያሰረዳችሁ ጠይቁ። ማሰተማር ምርጡ የመማሪያ መንገድ ነው።
- ከእያንዳንዱ ምዕራፍ በኋላ የፈተና ውጤቱን ተመልከቱ፤ ከፍተኛ ማርክን ብቻ ሳይሆን መሻሻልንም አበረታቱ።

ማውጫ

መነሻ	የመነሻ ፈተና · ከየት ልጀምር?	6
ምዕራፍ 1	የምሥራቅ አፍሪካ መገኛ	8
	ማጠቃለያ 17 · የፈተና ጥያቄዎች 18 · ለመምህሩ 20 · መልሶች 21	
ምዕራፍ 2	ሳይንስን መገንዘብ	23
	ማጠቃለያ 34 · የፈተና ጥያቄዎች 34 · ለመምህሩ 36 · መልሶች 37	
ምዕራፍ 3	የተፈጥሮ አካባቢ	40
	ማጠቃለያ 50 · የፈተና ጥያቄዎች 51 · ለመምህሩ 53 · መልሶች 53	
ምዕራፍ 4	ማኅበራዊ አካባቢ	56
	ማጠቃለያ 66 · የፈተና ጥያቄዎች 67 · ለመምህሩ 69 · መልሶች 70	
ምዕራፍ 5	ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች	72
	ማጠቃለያ 78 · የፈተና ጥያቄዎች 79 · ለመምህሩ 81 · መልሶች 82	
	የቁልፍ እውነታዎች ገጽ	84
	ብዙ ጊዜ የሚሠሩ 20 ስሕተቶች	86
	የፈተና ስልት	87
	ሞዴል ፈተና 1 · የመጀመሪያ ወሰነ ትምህርት (ምዕራፍ 1–3)	89
	ሞዴል ፈተና 2 · የዓመቱ ሙሉ (ምዕራፍ 1–5)	94
	ሞዴል ፈተና 3 · የዓመቱ ሙሉ (ምዕራፍ 1–5)	99
	የሞዴል ፈተናዎቹ መልሶች	104

የገጽ ቁጥሮቹ በእያንዳንዱ ገጽ ግርጌ ያሉትን ቁጥሮች (እና የPDF ገጽ ቁጥርን) ያመለክታሉ።

የመነሻ ፈተና · ከየት ልጀምር?

10 ጥያቄዎች · 15 ደቂቃ። ይህንን ፈተና መጽሐፉን **ከመጀመራችሁ በፊት** ሥሩ። ከእያንዳንዱ ምዕራፍ ሁለት ጥያቄዎች አሉ። ውጤቱ ጊዜያችሁን የት ማዋል እንዳለባችሁ ብቻ ያሳያል።

1. የምድር ወገብ ሰንት ዲግሪ ነው?

   ሀ. 90° **ለ.** 66½°

   ሐ. 23½° **መ.** 0°

2. የአፍሪካ ትልቁ ተራራ የቱ ነው?

   ሀ. ሩዋንዞሪ **ለ.** ራስ ደጀን

   ሐ. ኪሊማንጃሮ **መ.** ኬንያ ተራራ

3. ቁስል ሲያጋጥመን ደም እንዲረጋ የሚያደርገው የደም ክፍል የቱ ነው?

   ሀ. ፕላዝማ **ለ.** ፕሌትሌት

   ሐ. ነጭ የደም ህዋስ **መ.** ቀይ የደም ህዋስ

4. ውሃ ምን ዓይነት የጉልበት ምንጭ ነው?

   ሀ. የባትሪ ዓይነት **ለ.** ታዳሽ ያልሆነ

   ሐ. ታዳሽ **መ.** የሚያልቅ ነዳጅ

5. በኢትዮጵያ ዋናው የዝናብ ወቅት የትኛው ነው?

   ሀ. ከታኅሣሥ እስከ የካቲት **ለ.** ከጥር እስከ መጋቢት

   ሐ. በጥቅምትና በሚያዝያ ብቻ **መ.** ከሰኔ እስከ መስከረም

6. የአዋሽ ወንዝ የሚያበቃው የት ነው?

   ሀ. ሜዲትራኒያን ባሕር **ለ.** ሕንድ ውቅያኖስ

   ሐ. ቀይ ባሕር **መ.** አቤ ሐይቅ

7. የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ሰንት ናቸው?

   ሀ. 11 **ለ.** 36

   ሐ. 6 **መ.** 5

8. ለናይል ወንዝ ከፍተኛውን ውሃ የምታበረክተው ሀገር ማን ናት?

   ሀ. ሱዳን **ለ.** ኢትዮጵያ

   ሐ. ዩጋንዳ **መ.** ግብፅ

9. ኤች.አይ.ቪ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው በየትኛው መንገድ ነው?

ሀ. ያልተመረመረ ደም በመውሰድ
ለ. በመጨባበጥ
ሐ. በአንድ ክፍል በመማር
መ. አብሮ በመብላት

10. ድርቅ ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. ከፍተኛ ጎርፍ
ለ. ባልተለመደ ሁኔታ የዝናብ እጥረት
ሐ. የሕዝብ ብዛት መጨመር
መ. የሚበላ ምግብ መጥፋት

መልሶችና የጥናት ዕቅድ

ጥ	ምዕራፍ	መልስ	ምክንያት
1	1	መ	መነሻ መስመር
2	1	ሐ	5895 ሜ
3	2	ለ	ፕሌትሌት ያረጋል
4	2	ሐ	ፀሐይ፣ ንፋስ፣ ውሃ
5	3	መ	የሰሜናዊው ክፍል
6	3	መ	ከኢትዮጵያ አይወጣም
7	4	ሀ	11
8	4	ለ	86%
9	5	ሀ	በደም ንክኪ
10	5	ለ	ረሃብ = የምግብ እጥረት

ውጤታችሁን እንዴት ትጠቀሙበታላችሁ?

- **በአንድ ምዕራፍ ሁለቱንም በትክክል ከመለሳችሁ፦** «ተጠንቀቁ!» ሳጥኖቹን አንብቡ፤ በቀጥታ ወደ Exam Boosters፣ ወደ ደረጃ 2 እና 3 መልመጃዎችና ወደ ፈተናው ሂዱ።
- **አንዱን ብቻ ከመለሳችሁ፦** ምዕራፉን ከዋና ዋና ሐሳቦቹ ጀምራችሁ በተለመደው መንገድ ሥሩ።
- **ሁለቱንም ከተሳሳታችሁ፦** በዚያ ምዕራፍ ጀምሩ፤ ቀስ ብላችሁ አንብቡ፤ መፍትሔውን ከማንበባችሁ በፊት እያንዳንዱን ምሳሌ ራሳችሁ ሞክሩ።
- መጽሐፉን ሰትጨርሱ ይህንን ፈተና እንደገና ሥሩና ውጤታችሁን አወዳድሩ።

ምዕራፍ 1 · የምሥራቅ አፍሪካ መገኛ

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፦

- አቅጣጫዎችን ትለያላችሁ
- ኬክሮስንና ኬንትሮስን በመጠቀም የአንድን ቦታ ፍጹማዊ መገኛ ታገኛላችሁ
- የምሥራቅ አፍሪካን አንጻራዊና ፍጹማዊ መገኛ በካርታ ላይ ታሳያላችሁ
- የምሥራቅ አፍሪካን አጎራባች ሀገራትና ውሃማ አካላት ትዘረዝራላችሁ
- የክልሉን ዋና ዋና ተራሮች፣ ሐይቆችና ወንዞች ትለያላችሁ
- ጂፒኤስን፣ ጎግል ማፕንና ጎግል ኧርዝን ትለያላችሁ፤ ጥቅማቸውን ታውቃላችሁ

ከመጀመራችሁ በፊት — ራሳችሁን ፈትሹ። (ሀ) አራቱ ዋና ዋና አቅጣጫዎች ምን ምን ናቸው? (ለ) ፀሐይ የምትወጣው በየትኛው አቅጣጫ ነው? (ሐ) የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ማን ናት? (መ) ኢትዮጵያ የምትገኘው በየትኛው አህጉር ነው?
መልሶች፦ (ሀ) ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅ፣ ምዕራብ (ለ) በምሥራቅ (ሐ) አዲስ አበባ (መ) በአፍሪካ

ይህ ምዕራፍ በፈተና እንዴት ይመጣል?

በአዲስ አበባ የ6ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ሞዴል ፈተናዎች ውስጥ ደጋግመው የሚመጡ የጥያቄ ዓይነቶች፦

- "የኢትዮጵያ ፍጹማዊ መገኛ የቱ ነው?" (3°–15° ሰሜን ኬክሮስ እና 33°–48° ምሥራቅ ኬንትሮስ)
- በኬክሮስና በኬንትሮስ ፍርግርግ ላይ የአንድን ፊደል (ነጥብ) ፍጹማዊ መገኛ ማንበብ
- የሐሩር መስመሮችና ክበቦች ዲግሪ (የካፕሪኮርን መስመር፣ የአርክቲክ ክበብ…)
- "ምሥራቅ አፍሪካን የሚያዋስኑ ሀገራት ሰንት ናቸው?" እና "አጎራባች ያልሆነው የቱ ነው?"
- ትልቁ ተራራ (ኪሊማንጃሮ)፣ ትልቁ ውሃማ አካል (ሕንድ ውቅያኖስ)፣ ቪክቶሪያ ሐይቅን የሚጋሩ ሀገራት
- "በኢትዮጵያ የማይገኘው ወንዝ የቱ ነው?" እና በአንድ ሀገር የሚገኝ የቱሪስት መስህብ
- የጂፒኤስ፣ የጎግል ማፕና የጎግል ኧርዝ ልዩነት


ከ40 የፈተና ጥያቄዎች ውስጥ በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ፈተና ከ12 እሰከ 15፣ በሁለተኛው ደግሞ ከ5 እሰከ 8 የሚሆኑት ከዚህ ምዕራፍ ይመጣሉ።

ቁልፍ ቃላት፦ አቅጣጫ (direction) · አንጻራዊ መገኛ (relative location) · ፍጹማዊ መገኛ (absolute location) · ኬክሮስ (latitude) · ኬንትሮስ (longitude) · የምድር ወገብ (equator) · ግሪንዊች — መነሻ ኬንትሮስ (prime meridian) · ንፍቀ ክበብ (hemisphere) · አጎራባች (neighbour) · ውሃማ አካል (water body) · ሰምጥ ሸለቆ (rift valley) · ጂፒኤስ (GPS) · ጎግል ማፕ (Google Maps) · ጎግል ኧርዝ (Google Earth)

1.1 የምሥራቅ አፍሪካ መገኛ በካርታ ላይ

ዋና ዋና ሐሳቦች


- **አራቱ ዋና አቅጣጫዎች፦** ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅ፣ ምዕራብ። በመካከላቸው ያሉት፦ ሰሜን ምሥራቅ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምሥራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ።
- **አንጻራዊ መገኛ** አንድ ቦታ **ከሌሎች ቦታዎች አንጻር** የት እንደሚገኝ ይገልጻል። ለምሳሌ "ኬንያ ከኢትዮጵያ በሰተ ደቡብ ትገኛለች።"
- **ፍጹማዊ መገኛ** አንድ ቦታ በ**ኬክሮስና በኬንትሮስ** መሰመሮች የሚገኝበት ትክክለኛ ቦታ ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ከ3° እሰከ 15° ሰሜን ኬክሮስ እና ከ33° እሰከ 48° ምሥራቅ ኬንትሮስ መካከል ትገኛለች።
- **አግድም (ትይዩ) መሰመሮች (parallels)** በካርታ ወይም በሉል ላይ **ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ** የተሰመሩ የሐሳብ መሰመሮች ናቸው። መነሻቸው የምድር ወገብ (0°) ነው፤ በሰተ ሰሜን 90፣ በሰተ ደቡብ 90 — በአጠቃላይ **180** አግድም መሰመሮች አሉ። ሁሉም ትይዩ ናቸው፤ አይገናኙም። በእነሱ የሚለካው ማዕዘናዊ ርቀት **ኬክሮስ** ይባላል።
- **ቋሚ (የማገር) መሰመሮች (meridians) ከሰሜን ወደ ደቡብ** የተሰመሩ ናቸው። መነሻቸው **ግሪንዊች (ፕራይም) ሜሪዲያን** (0°) ነው፤ በሰተ ምሥራቅ 180፣ በሰተ ምዕራብ 180 — በአጠቃላይ **360** ቋሚ መሰመሮች አሉ። ሁሉም በሰሜንና በደቡብ ዋልታ ይገናኛሉ። በእነሱ የሚለካው ማዕዘናዊ ርቀት **ኬንትሮስ** ይባላል።
- እነዚህ መሰመሮች በካርታና በሉል ላይ ብቻ ይገኛሉ፤ በመሬት ላይ እናያቸውም።
- **የምድር ወገብ (0°)** ምድርን ለ**ሰሜንና ለደቡብ ንፍቀ ክበብ** ይከፍላል። **ግሪንዊች (0°)** ደግሞ ለ**ምሥራቅና ለምዕራብ ንፍቀ ክበብ** ይከፍላል።
- **አምስቱ ዐበይት ትይዩ መሰመሮች (ምሰል 1.1)፦** የምድር ወገብ 0° · የካንሰር መሰመር 23½° ሰሜን · የካፕሪኮርን መሰመር 23½° ደቡብ · የአርክቲክ ክበብ 66½° ሰሜን · የአንታርክቲክ ክበብ 66½° ደቡብ
- **ፍጹማዊ መገኛን ሰትጽፉ** መጀመሪያ ኬክሮሱን (ሰሜን/ደቡብ)፣ ቀጥሎ ኬንትሮሱን (ምሥራቅ/ምዕራብ) ጻፉ።



ምስል 1.1 — ዋና ዋና የኬክሮስ መስመሮችና ግሪንዊች

ምሥራቅ አፍሪካ

- አፍሪካ በአምስት ቀጠናዎች ይከፈላል፦ ምሥራቃዊ፣ መካከለኛው፣ ሰሜናዊ፣ ደቡባዊ እና ምዕራባዊ አፍሪካ። ምሥራቅ አፍሪካ ከአፍሪካ የቆዳ ስፋት **21%** ይሸፍናል፤ በስፋቱ **ሦስተኛ** ነው።
- **የምሥራቅ አፍሪካ ፍጹማዊ መገኛ፦** ከ18° ሰሜን እስከ 27° ደቡብ ኬክሮስ፣ እንዲሁም ከ22° ምሥራቅ እስከ 51°28′ ምሥራቅ ኬንትሮስ።
- በመማሪያ መጽሐፋችን መሠረት ምሥራቅ አፍሪካ **19 ሀገራትን** ይይዛል። ዋና ዋና ንዑስ ክልሎቹ (ምስል 1.2)፦
- **የአፍሪካ ቀንድ፦** ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ጂቡቲ፣ ሶማሊያ
- **የታላላቅ ሐይቆች አካባቢ፦** ኬንያ፣ ዩጋንዳ፣ ታንዛንያ፣ ሩዋንዳ፣ ቡሩንዲ
- **የሕንድ ውቅያኖስ ደሴቶች፦** ኮሞሮስ፣ ሪዩኒየን፣ ሲሸልስ፣ ሞሪሸየስ፣ ማዳጋስካር (ማዳጋስካር የአፍሪካ ትልቁ ደሴት ነው)
- መጽሐፉ በስንጠረዥ የሚጠቅሳት ሌላ ሀገር፦ ማላዊ
- **የምሥራቅ አፍሪካ አንጻራዊ መገኛ፦** በሰሜን የሰሜን አፍሪካ ሀገራትና ቀይ ባሕር · በምሥራቅ የኤደን ባሕረ ሰላጤና ሕንድ ውቅያኖስ · በደቡብ ደቡብ አፍሪካ · በምዕራብ የመካከለኛው አፍሪካ ሀገራት ይገኛሉ።
- ኢትዮጵያ በ**አፍሪካ ቀንድ** ውስጥ ትገኛለች። አጎራባቾቿ፦ በሰሜን ኤርትራ · በሰሜን ምሥራቅ ጂቡቲ · በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ ሶማሊያ · በደቡብ ኬንያ · በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ ደቡብ ሱዳን · በሰሜን ምዕራብ ሱዳን።



ምስል 1.2 — ምሥራቅ አፍሪካ፣ ንዑስ ክልሎቹና አዋሳኝ ሀገራት (ደሴቶቹ ትንንሽ ስለሆኑ በስማቸው ብቻ ተመልክተዋል)

ምሳሌ 1.1 — አንጻራዊ ወይስ ፍጹማዊ?


እያንዳንዱ ዓረፍተ-ነገር አንጻራዊ መገኛን ነው ወይስ ፍጹማዊ መገኛን የሚገልጸው?
(ሀ) ጂቡቲ ከኢትዮጵያ በስተ ስሜን ምሥራቅ ትገኛለች። (ለ) ኢትዮጵያ ከ3° እስከ 15° ስሜን ኬክሮስ እና ከ33° እስከ 48° ምሥራቅ ኬንትሮስ መካከል ትገኛለች። (ሐ) ኬንያ ከሕንድ ውቅያኖስ በስተ ምዕራብ ናት።

መፍትሔ። (ሀ) **አንጻራዊ** — ከኢትዮጵያ አንጻር ነው። (ለ) **ፍጹማዊ** — ዲግሪዎችን ይጠቀማል። (ሐ) **አንጻራዊ** — ከሕንድ ውቅያኖስ አንጻር ነው።
ዘዴ፦ ዓረፍተ-ነገሩ **ዲግሪ (°)** ካለው ፍጹማዊ ነው፤ "በስተ … " ብቻ ካለው አንጻራዊ ነው።

ምሳሌ 1.2 — Exam Booster 1A · የኢትዮጵያ ፍጹማዊ መገኛ

የኢትዮጵያ ፍጹማዊ መገኛ የቱ ነው?
ሀ. ከ3° እስከ 15° ሰሜን ኬክሮስ እና ከ33° እስከ 48° ምሥራቅ ኬንትሮስ
ለ. ከ33° እስከ 48° ሰሜን ኬክሮስ እና ከ3° እስከ 15° ምሥራቅ ኬንትሮስ
ሐ. ከ3° እስከ 15° ደቡብ ኬክሮስ እና ከ33° እስከ 48° ምዕራብ ኬንትሮስ
መ. ከ12° እስከ 18° ሰሜን ኬክሮስ እና ከ36° እስከ 44° ምሥራቅ ኬንትሮስ

መፍትሔ። ኢትዮጵያ ከምድር ወገብ በሰተ **ሰሜን**፣ ከግሪንዊች በሰተ **ምሥራቅ** ትገኛለች። ኬክሮሱ (3°–15°) ትንሹ ክልል ነው፤ ኬንትሮሱ (33°–48°) ትልቁ ነው። **መልሱ ሀ ነው።**
ለ ቁጥሮቹን አገላብጧል፤ ሐ አቅጣጫዎቹ ተሳስተዋል።
አሰታውሱ፦ **"3–15 ሰሜን፣ 33–48 ምሥራቅ"**



ምስል 1.3 — የኬክሮስና የኬንትሮስ ፍርግርግ (ቀዩ የምድር ወገብ፣ አረንጓዴው ግሪንዊች ነው)

ምሳሌ 1.3 — Exam Booster 1B · ፍርግርግ ማንበብ

በምስል 1.3 ላይ የፊደላቱን ፍጹማዊ መገኛ ጻፉ።

መፍትሔ። መጀመሪያ ኬክሮሱን (ከቀዩ መስመር በላይ ወይም በታች)፣ ቀጥሎ ኬንትሮሱን (ከአረንጓዴው መስመር በቀኝ ወይም በግራ) አንብቡ፦

ፊደል	ኬክሮስ	ኬንትሮስ
ሀ	10° ሰሜን	20° ምሥራቅ
ለ	20° ሰሜን	10° ምዕራብ
ሐ	20° ደቡብ	10° ምሥራቅ
መ	10° ደቡብ	20° ምዕራብ